## የዘመነውን የ 2023-2024

# የ COVID-19 ክትባት ያግኙ

CDC እድሜው 6 ወር እና ከዚያ በላይ የሆነው እያንዳንዱ ሰው የዘመነውን የ2023–2024 የ COVID-19 ክትባት እንዲወስድ ይመክራል። ሶስት ክትባቶች ቀርበዋል፡- Pfizer፣ Moderna ወይም Novavax (እድሜያቸው 12 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ) እና ሁሉም በ COVID-19 ከሚመጣ የጠና ህመም ይከላከላሉ።

አንዱ ክትባት ከሌላው ይሻላል ተብሎ አይመከርም። ለእርስዎ የተዘጋጀ እንዲሁም ለእድሜዎ ተስማሚ የሆነ ክትባት ሊወስዱ ይገባል። ከዚህ በፊት ከወሰዱት ዶዞች የተለየ የክትባት የምርት ስም ማግኘት ምንም ችግር የለውም።

| እድሜው ከ 6 ወር እስከ 4 አመት | እድሜው ከ 5 እስከ 11 አመት | እድሜ 12 እና ከዚያ በላይ — ያልተከተበ | እድሜ 12 እና ከዚያ በላይ — የተከተበ |
|---|---|---|---|
| ቢያንስ **1** የዘመነ የ COVID-19 ክትባት ዶዝ (ወቅታዊ ለመሆን ብዙ ዶዞች ሊያስፈልጉ ይችላሉ) | **1** የዘመነ የ COVID-19 ክትባት | **1** የዘመነ Pfizer ወይም የዘመነ Moderna የ COVID-19 ክትባት **ወይም** **2** ዶዝ የዘመነ የ Novavax COVID-19 ክትባት | **1** የዘመነ የ COVID-19 ክትባት |

COVID-19 ን የሚያመጣው ቫይረስ ሁል ጊዜ እየተቀያየረ ሲሆን ከዚህ በፊት ከነበሩ የ COVID-19 ክትባቶች የሚገኘው ጥበቃ በጊዜ ሂደት እየቀነሰ ነው። የዘመነ የ COVID-19 ክትባት ማግኘት ጥበቃን ወደነበረበት የሚመልስ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እየተሰራጩ ካሉ የተለያዩ ቫይረሶች የተሻሻለ ጥበቃ ይሰጣል።

**!** ዕድሜያቸው 65 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የዘመነውን የ COVID-19 ክትባት ተጨማሪ ዶዝ መውሰድ አለባቸው። በሽታ የመከላከል አቅማቸው በመጠነኛ ወይም በከባድ ደረጃ የተዳከሙ ሰዎች ተጨማሪ ዶዞች ሊወስዱ ይችላሉ። የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

የዘመነ የ 2023-2024 የ COVID-19 ክትባትን በሚመለከት ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ ወይም ለበለጠ መረጃ ስለ COVID-19 ክትባት (www.health.mn.gov/diseases/coronavirus/vaccine/basics.html) ወይም CDC:- በ COVID-19 ክትባቶች ወቅታዊ ሆነው ይቆዩ (www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/vaccines/stay-up-to-date.html) የሚለውን ይጎብኙ።

የሚኒሶታ የጤና መምሪያ | health.mn.gov | 625 Robert Street North PO Box 64975, St. Paul, MN 55164
651-201-5000 |ምትክ ቅርጸት ለመጠየቅ health.communications@state.mn.usን ያነጋግሩ።

04/29/2024

MINNESOTA